# መስከረም 14/1998 ዓ.ም ከተዋሃደው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ

## ‹‹የፓርቲው ስም ስለተቀማ ሕዝብ ትግሉን ያቆማል ማለት አይደለም››

በ1997 ዓ.ም በተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ የምረጡን ቅስቀሳ ያካሄድንበት፣ ለፌዴራልና ለክልል ምክር ቤቶች የተወዳደርንበት፣ የተመረጥንበት፣ የታሠርንበት፣ የተከሰስንበት እንዲሁም አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን የሞቱበት፣ የታሠሩበት፣ አካለ ስንኩል የሆኑበት፣ ከሥራ፣ ከቤትና ከንብረታቸው የተፈናቀሉበትና የተሰደዱበት ፓርቲ፣ ስሙና ዓርማው በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለሌላ አካል በመስጠቱ ሚያዚያ 8/2000 ዓ.ም ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በምርጫ ቦርድ ላይ ክስ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ መስከረም 14/1998 ዓ.ም በአራት ፓርቲዎች ውኅደት መፈጸሙና የአራቱም ፓርቲዎች ሊቀመናብርት ይህንኑ በፊርማቸው ማረጋገጣቸው ይታወሳል፡፡ ሰነዱም ለምርጫ ቦርድ በወቅቱ ቀርቧል፡፡ ነገር ግን ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የቅንጅት አመራር አባላት እስር ቤት በነበርንበት እና ተገቢውን ምላሽ ልንሰጥ በማንችልበት ሰዓት በፓርቲነት ለመመዝገብ የሚያስችል ሰነድ አሟልታችሁ አቅርቡ ማለቱም አይዘነጋም፡፡

እኛም ከእስር ከተፈታን በኋላ አላግባብ ለሌላ የተሰጠብን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ስያሜና ዓርማ እንዲመለስልን ለማድረግ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ከሰን ከሚያዚያ 8/2000 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 16/2000 ዓ.ም በፍርድ ቤት ክርክር ተካሂዷል፡፡

በዚሁ መሠረትም ሐምሌ 16/2000 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 9ኛ ፍትሐ ብሔር ችሎት በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ስያሜና አርማ ለመጠቀም እንደማንችል ወስኖብናል፡፡

እኛ ወደ ፍርድ ቤት የሄድነው የሕጉን መንገድ እስከ መጨረሻው ለማየት ነበር፡፡ ከቀረበው የክስ ይዘት ጋር የማይጣጣም ውሳኔ ቢሰጥም እኛ በዚህ ውሳኔ ሳንደናገጥ ትግላችን በበለጠ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ፓርቲያችን የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሙ የገነባው ድርጅት በመሆኑ የሕዝብ ሃብት ነው፡፡ ሕዝቡ ስሙን ስለተከለከለ ትግሉን ያቆማል ማለት አይደለም፡፡

ትግሉ ውጤታማ የሚሆነው በሕዝቡ ትግል እንጂ በፓርቲ ስያሜ ብቻ አይደለም:: ስለዚህ ትናንት ይዘነው የተነሳነውን ዓላማ ዛሬም ከግብ ለማድረስ ጠንክረን እንሠራለን:: ዛሬም ለፍትሕና ለዴሞክራሲ መስፈን እንታገላለን::

መስከረም 14/19998 ዓ.ም ውህደት የፈፀምነው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራር አባላት ከእስር ከመፈታታችን በፊት በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት በተካሄደው ውይይት ከእስር ከተፈታን በኋላም በነበረን ፓርቲ ለመቀጠል እንደምንችልም ከመንግሥት የተገባልን ቃል እንደነበረም ለፍርድ ቤቱ አቅርበናል:: ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ለዚህ ቃል ይሁንታ ሳያሳይ የሰጠን ውሳኔ የተገባልን ቃል ሳይከበር መቅረቱን በዛሬው ዕለት አስገንዝበናል::

ፓርቲያችን 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን ከሰኔ 14-15/2000 ዓ.ም ማካሄዱ ይታወቃል:: በጉባዔው ላይ ስማችንና አርማችንን ለማስመለስ የሚደረገው የፍርድ ቤት ሂደት ውጤቱ እንደታወቀ ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ የፓርቲውን ተለዋጭ ስምና ዓርማ አዘጋጅቶ ለምርጫ ቦርድ እንዲያቀርብ ውክልና የሰጠ መሆኑ ይታወሳል:: ይህንንም ውሳኔ ጠቅላላ ጉባዔው ባወጣው የአቋም መግለጫ ላይ አረጋግጧል::

የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ አባላትም ከፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ በተሰጠን ውክልና መሠረት ለፓርቲያችን ስምና ዓርማ አዘጋጅተን ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምናቀርብ መሆኑን ለተከበራችሁና ለተወደዳችሁ የፓርቲያችን አባሎች፣ ደጋፊዎችና በአጠቃላይ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ለምትኖሩ ለኢትዮጵያውያን እንገልጻለን::

ሰላማዊ ትግላችን ይቀጥላል

ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ ይሰፍናል::

ኃይሉ ሻውል

የፓርቲው ፕሬዚዳንት